# Grenfell Tower community update: July 2026 - Amharic / አማርኛ

**የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ፡- ጁላይ 2026**
ግሬንፌል ታወር በአደጋው ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ጥልቅ የሆነ የግል ትርጉም እንዳለው እና በታው ለቤተሰቦች የተከበረ መሆኑን እንረዳለን።

ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ስራ እየሰራን እያለ ወቅታዊ መረጃዎችን ልናጋራዎ እንወዳለን። በዚህ ወቅታዊ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡-

- **የዕቅድ ማመልከቻ**
- **የታወሩን መጠቅለያ መተካት**
- **ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ብክለት የሚደረግ ክትትል መረጃ**
- **የጤና እና ደህንነት ድጋፍ**
- **እኛን ለማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች**

ቀደም ሲል የወጡ መረጃዎችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡-
www.gov.uk/grenfell-community-updates

## የታወሩን መጠቅለያ መተካት

የግሬንፌል የልብ ምልክት ባነሮች፣ ከአደጋው የዘጠኝ ዓመት ክብረ በዓል በኋላ ከታወሩ ላይ በጥንቃቄ ተነስተው በጥሩ ቦታ ላይ ተቀምጠዋል። ታወሩን ከአስቸጋሪ አየር ሁኔታ ለመከላከል ሲባል ከባነሮቹ ጀርባ የነበረው ነጭ መጠቅለያ፣ በአሁኑ ጊዜ
በመተካት ላይ ይገኛል።

## የዕቅድ ማመልከቻ

የግሬንፌል ታወርን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራ ባለፈው ዓመት የተጀመረው 'ፈቃድ የሚጠይቅ ግንባታ' (Permitted Development) በሚል መጠሪያ በሚታወቅ የዕቅድ ፈቃድ ሲሆን፣ ይህም ለ12 ወራት የሚቆይ ነው። ለቀረው ስራ በክራውን ልማት ዕቅድ (Crown Development planning route) በኩል ማመልከቻ አቅርበናል። ይህ በሂደቱ ውስጥ የሚከናወን ቀጣይነት ያለው መደበኛ እርምጃ ሲሆን፣ ሥራው የሚከናወንበትን አኳኋን አይለውጥም።

የማመልከቻውን ዝርዝር በሚከተለው ሊንክ ማንበብ ይችላሉ፡-
CROWN/2026/0000003 - ሰነዶች – የክራውን ልማት ማመልከቻን (Crown Development Application) ያግኙ

ይህ ሂደት በ'ፍሪሃውስ' (Freehaus) እየተመራ ካለውና በማኅበረሰቡ አስተያየት ላይ ከተመሠረተው የዲዛይን ሂደት በኋላ፣ በዚህ ዓመት መጨረሻ ላይ ለግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) መታሰቢያ ከሚቀርበው የዕቅድ ማመልከቻ የተለየ ነው።

## ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና ጫጫታ የሚደረግ ክትትል መረጃ

መንግሥት በግሬንፌል ታወር ጣቢያ የሚከናወኑ ማናቸውም ሥራዎች በከፍተኛ ጥራት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። የማህበረሰቡ እና በጣቢያው ላይ የሚሰሩ ሰዎች ደህንነት እና ጤንነት ሁልጊዜም ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው። በጣቢያው ላይ ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ጫጫታ የቀጥታ መረጃዎችን የሚሰበስቡ የክትትል መሣሪያዎች ተተክለዋል። መረጃው በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቶችን ለማየት፣ እባክዎን ከታች ያሉትን አገናኞች ይጫኑ፡-

የአቧራ ቁጥጥር ሪፖርት ከሜይ 4 እስከ ሜይ 31 2026 የንዝረት ቁጥጥር ሪፖርት ከሜይ 4 እስከ ሜይ 31 2026 የድምጽ ብክለት ቁጥጥር ሪፖርት ከሜይ 4 እስከ ሜይ 31 2026

የእንግሊዝ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ (UK Health Security Agency, UKHSA) ሥራው በሚካሄድበት ጊዜ በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ዙሪያ ያለውን የአየር ጥራት መገምገምና መከታተልን ይቀጥላል። ሪፖርቶቹ በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋሉ። የቅርብ ጊዜውን ሪፖርት እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡-
የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) እሳትን ተከትሎ የሚደረግ የአካባቢ ክትትል - GOV.UK

## የጤና እና ደህንነት ድጋፍ

ማንኛውንም ሰው አነጋግረው መወያየት ከፈለጉ፣ የግሬንፌል ጤና እና ደህንነት አገልግሎት (Grenfell Health and Wellbeing Service) ለሕፃናትም ሆነ ለአዋቂዎች ነፃ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ የNHS አገልግሎት ነው። ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ፣ ቤተሰባቸውን ላጡ፣ ከአደጋው በሂወት ለተረፉት እና በአቅራቢያው ለሚገኙ ነዋሪዎች የሥነ-ልቦና እና የአካል ደህንነት ድጋፍ መሰጠቱ ይቀጥላል። አንድ ሰው ማነጋገር ከፈለጉ፡-

- በ 020 8637 6279 ለግሬንፌል ደህንነት አገልግሎት (Grenfell Wellbeing Service) ይደውሉ (በየቀኑ ከ8am እስከ 8pm)።
- ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም የማዕከላዊ እና የሰሜን ምዕራብ ለንደን የኤን ኤች ኤስ ፋውንዴሽን ትረስት (Central and North West London NHS Foundation Trust's, CNWL) የአንድ ጊዜ የምክር አገልግሎት መስመርን በሚከተለው አድራሻ ይደውሉ፡- 0800 0234 650 (በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው)።
- ኢሜይል፡- grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ተጨማሪ ለማወቅ እዚህ ይጎብኙ፡- www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk

ስለሚገኙ አገልግሎቶች የቅርብ ጊዜ መረጃ ለማግኘት www.grenfell.nhs.ukን ይጎብኙ

## እኛን ለማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች

መረጃዎችን ለእርስዎ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ማካፈል እንፈልጋለን። በሚከተሉት አድራሻዎች ላይ በየጊዜው የሚወጡ ዝማኔዎችን እና መረጃዎችን ማጋራታችንን እንቀጥላለን፡-
www.gov.uk/grenfell-community-updates

እባክዎ በዚህ ኢሜይል ያድርጉልን፦ GrenfellTowerSite@communities.gov.uk ወደ፦

- እኛን ወይም የቦታው ዋና ሥራ ተቋራጭ የሆነውን DCUK ለማነጋገር ቀጥሮ ይያዙ።
- ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራን በተመለከተ ያሉዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች ይጠይቁን ወይም ስጋቶችዎን ያነጋሩን።
- የምናወጣቸው ወቅታዊ መረጃዎች በቀጥታ በኢሜይል እንዲላኩልዎ ይጠይቁን።
- ከእርስዎ ጋር በምናደርገው የግንኙነት እና የተሳትፎ ሂደት ላይ ያለዎትን አስተያየት፣ ፍላጎትዎ ከሆነ፣ ያጋሩን። የእርስዎን ሃሳቦች በደስታ እንቀበላለን።

ስለ ግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘት እና የኢሜይል ማሳወቂያዎች እንዲደርስዎ ለመመዝገብ፣ እባክዎን ወደ www.gov.uk/grenfell-community-updates ይሂዱ ወይም የQR ኮዱን ይቃኙ።